# መመሪያ-ደንብ

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ

**ተዛማጅ ግብአቶች፡-** ACF, ACF-RA, COB-RA, IJA-RA, IOH-RA, IRB-RA, JHC, JHF, JHF-RA, JOA-RA

**ኃላፊ ጽ/ቤት፡-** ዋና የሥራ ኃላፊ
Chief Academic Officer የአካደሚ ዋና ኃላፊ
Chief of School Support and Improvement
የትምህርት ቤት ድጋፍ እና ማሻሻል ዋና ኃላፊ
Chief Operating Officer ዋና የሥራ ኃላፊ

## የልጅ መጎሣቆል እና ቸልተኝነትን ሪፖርት ማድረግና መመርመር

I. **ዓላማ**

ስለ ልጅ ጉስቁልና እና ቸልተኝነትን ማስታወቅና መመርመር ቅደም ተከተሎችና መመርያዎች

II. **ትርጓሜዎች**

A. ማጎሳቆል ማለት –

1. የአንድ ልጅ ወይም ደካማ አዋቂ፣ ማንኛውም ሊታይ ወይም ላይታይ የሚችል አካላዊ ጉዳት፣ ወይም የአእምሮ ጉዳት፣ ልጁን/ልጅቷን ወይም ደካማ አዋቂውን/ዋን የመንከባከብ ጊዜያዊ ወይም ዘላቂ ጠባቂነት ወይም ሃላፊነት ባለው/ላት በማንኛውም ግለሰብ፣[1] የልጁ/ጅቷ ወይም የደካማው/ዋ አዋቂ ጤና ወይም ደህንነትን በጉዳት ላይ መጣል ወይም የተጨበጠ የመጎዳት አደጋ ላይ መሆኑን በሚያመለክት ሁኔታ መፈፀም።

2. ልጅን ወይም ደካማ አዋቂን የመንከባከብ ዘላቂ ወይም ጊዜያዊ ጠባቂነት ወይም ሃላፊነት ባለው/ባላት በማንኛውም ግለሰብ በልጅ ወይም በደካማ አዋቂ ላይ የተፈፀመ ማንኛውም የፆታዊ ጥቃት ተግባር ወይም ተግባሮች (አካላዊ ጉዳቶች ይድረስም አይድረስም)፣ የፆታዊ አደጋ ወይም ብዝበዛ የሚያካትት፣ የዘመድ የፆታ ግንኙነት፣ መዳፈር፣ ወይም በማንኛውም ደረጃ የፆታ ጥቃት፣ ግብረ ሶዶም ወይም ከተፈጥሮ ውጭ የፆታዊ ጥቃት ልምምዶችን የሚጨምር ነገር ግን በነዚህ ያልተወሰነ። የወሲባዊ/ጾታዊ ትንኮሳ ወይም ብዝበዛን የሚያካትተው በዚህ አይገደብም፤ ከትንሽ ልጅ ወይም ተጋላጭ ከሆነ(ች) ጎልማሣ ጋር የሚደረግ የግብረስጋ ንኪኪ፣ እርቃንን በማሳየት ወይም የሌሎችን ብልት እያዩ ወይም ሌሎች የሚያደርጉትን የግብረስጋ ግንኙነትን እየተመለከቱ ስሜትን ማርካት/voyeurism፣ ወሲብ ለመፈጸም ማስገባት፣ መሣም ወይም መደባበስ/ማሻሸት፣ ለግብረስጋ ድርጊት መግራት፣ በማንኛውም ደረጃ የግብረስጋ ወንጀል መፈጸም፤ አስገድዶ በመድፈር፣ በሰገራ መጸዳጃ ቀዳዳ ወይም በአፍ/ተፈጥሮአዊ ባልሆነ ሁኔታ ግብረስጋ መፈጸም፣ ወይም ሽርሙጥና፣ መፍቀድ፣ ማደፋፈር፣ ወይም በነውር/ፀያፍ ድርጊት መሣተፍ፣ ወይም ወሲብ ቀስቃሽ ምስል/ስዕል ማሳየት፣ ብልት ፎቶግራፍ ማንሣት፣ በፊልም መቅረጽ፣ ወይም በህግ በተከለከለ ሁኔታ የልጅ ወይም ተጋላጭ ጎልማሳ ጾታዊ አካል በስዕላዊ ገለጻ ማሣየት፣ ለግብረስጋ ንግድ ዝውውር ማድረግ፣ ወይም ትንሽ ልጅ ወይም ተጋላጭ ጎልማሳን ከጾታ ጥቃት ወንጀለኛ

[1] ቋሚ ወይም ጊዝያዊ ጥበቃ ወይም ልጅን ወይም ደካማ አዋቂን የመንከባከብ ሃላፊነት ያለው ግለሰብ ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ ቤተሰብ ወይም ከቤተሰብ ጋር አብሮ የሚኖር፣ ጎረቤት፣ የMCPS ሰራተኛ፣ በጎ-ፈቃደኛ ወይም ስራ ተቋራጭ፣ በስልጣን ላይ የሚገኝ ግለሰብ፣ ወይም ሌላ ግለሰብን ያካትታል።

ጋር እንዲኖር/እንድትኖር ወይም ዘወትር በሚገኝበት/በምትገኝበት አኳኋን እንዲጋለጡ ማድረግ የመሣሠሉትን ያካትታል።

B. ሊጅማንኛውም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪ፣ የልጁ/ልጅቱ እድሜ የቱንም ያህል ቢሆን፣ እና እድሜው(ዋ) ከ18 ዓመት በታች የሆነ(ች) ማንኛውም ሌላ ሰው። የሜሪላንድ ህግ ባጠቃላይ እድሜው/ዋ ከ18 በላይ በሆነ ተማሪ ላይ የሚደርስን ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ባይወነጅልም፣ MCPS የዚህ ኣይነቱ ስነምግባር ከዚህ በታች በተቀመጡት ቅደም-ተከተሎች በመጠቀም ዘገባ እዲደረግ ይጠብቃል።

C. County Multi-Disciplinary Team/ከካውንቲው ባለብዙ ፈርጅ ድርጅቶች የተውጣጣ ቡድን (MDT) እንደኣግባቡ እየተገናኘ ምክርና የተቀነባበረ የህክምና ፕላን ዝግጅት የሚያደርግ የ Montgomery County ወኪል ድርጅቶች የባለሙያዎች ቡድን ነው። የካውንቲ MDT የ Montgomery County Tree House Child Assessment Cente/የትሪ ሃውስ የልጅ ግምገማ ማእከል እና የሚከተሉት የ Montgomery County ወኪል ድርጅቶች ተወካዮችን ያካትታል፦

1. The Montgomery County State's Attorney's Office/የስቴት ኣቃቤ ህግ ፅ/ቤት

2. The Special Victims Investigative Division of the Montgomery County Police Department/የፖሊስ መምርያ (MCPD) የልዩ ተጠቂዎች ምርመራ ክፍል

3. Child Welfare Services in the Montgomery County Department of Health and Human Services/በጤናና ሰብኣዊ እገልግሎቶች የልጅ ደህንነት ኣገልግሎቶች፣ በኣብዛኛው Child Protective Service/የልጅ ደህንነት ኣገልግሎት (CPS) ተብሎ የሚታወቀው፣ ወይም Aging and Disabilities Services Information and Assistance Unit in the Montgomery County Department of Health and Human Services/በጤናና ሰብኣዊ እገልግሎቶች ውስጥ የእርጅና እና የአካለስንኩላን ኣገልግሎቶች መረጃና እርዳታ ክፍል፣ በኣብዛኛው Adult Protective Services/የዓዋቂ ጥበቃ ኣገልግሎቶች (APS) ተብሎ የሚታወቀው፣ በደካማ ኣዋቂዎች ጉዳይ

ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት የተባሉ ጉዳዮች ተከሳሽ የ MCPS ሰራተኛ፣ የስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ የሆነበት/ችበት፣ የ MCPS ስርኣት-ኣቀፍ የልጅ መጎሳቆል ጉዳይ ተጠሪ ፣ ወይም ተወካይ፣ መወሰድ ያለበትን ተገቢ እርምጃ ለመወሰን፣ እንዲሁም በክውነውቶች ለመወያየት እና የተገኙ ትምህርቶችን እና የቀጣይ መሻሻል እድሎችን ለመገምገም የካውንቲ MDT ስብሰባዎችን እንዲከታተሉ ሊጋበዙ ይችላሉ።

በተጨማሪ፣ ትምህርት ቤትን-መሠረት ያደረገ የልጅ ጉስቁልና ሊኤይዞን-ሠራተኛ/Liaison ወይም ሌላ የ MCPS ሠራተኛ ሪፖርቱ ላይ ለተጠቀሰ(ች)ው ተማሪ የተቀናጀ እገልግሎት ለመስጠት ይቻል ዘንድ የካውንቲ MDT ስብሰባ ላይ እንዲሳተፍ/እንድትሳተፍ ይጋበዛል/ትጋበዛለች። መረጃዎች፣ ዘገባዎች፣ እና በካውንቲ MDT ኣማካይነት የተጋሩ ዘገባዎች በሁሉም ተሳታፊዎች በጥብቅ በሚስጢራዊነት መያዝ ኣለባቸው እናም በሜሪላንድ ህግ መሰረት ሳይፈቀድ እንዳይጋለጡ መጠበቅ ኣለባቸው።

D. ቤተሰብ ወይም የቤተሰብ ኣባል ማለት፣ መጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት በተፈጸመበት ወቅት፣ በልጁ ወይም ደካማ ኣዋቂ መኖርያ ቤት ኣብሮ የሚኖር፣ ወይም ዘወትር የሚገኝ ግለሰብ ማለት ነው። በመኖርያ ቤት መደበኛ ህላዌ ማለት የኣንድ ልጅ፣ ወይም የደካማ ኣዋቂ፣ ወይም የቤተሰብ ህይወት ትርጉም ያዘለ ኣካል የሚያደርገው ብቃት ካለው ብዛት ጋር የመኖርያ ቤት ጉብኝት ወይም ቆይታ ማለት ነው።

E. ትንሽ ልጅ ወይም ተጋላጭ ጎልማሣን ለግብረስጋ ተግባር መግራት ማለት፦ ከትንሽ ልጅ ወይም ተጋላጭ ጎልማሳ ጋር ስሜታዊ ግንኙነት/ዝንባሌ በመፍጠር ትንሽ ልጅ ወይም ተጋላጭ ጎልማሳን ለወሲባዊ ግንኙነትን ለመቀበል ፈቃደኛ እንዲሆን/እንድትሆን ማዘጋጀት ማለት ነው።

F. የአእምሮ ጉዳት/ቁስልማለት በትንሽ ልጅ ወይም ተጋላጭ ጎልማሣ አእምሮ ወይም ስነ-ልቡና የመሥራት ችሎታ ላይ የሚደርስ የሚታይ፣ ተለይቶ የሚታወቅ፣ እና ተጨባጭ/ትልቅ የሆነ ስንኩልነት/ድክመት ማለት ነው።

G. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ሠራተኞች/ MCPS Employees ማለት በ MCPS የተቀጠሩ ተተኪ አስተማሪዎችን ጨምሮ ሠርተፊኬት ያላቸው እና የሌላቸው ሰዎች ናቸው።

H. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ንብረት/MCPS Property ማለት በ MCPS ይዞታነት ያለ/ወይም የሚጠቀምበት መሬትን ጨምሮ ማንኛውም ትምህርት ቤት ወይም ፋሲሊቲ፣ እና የ MCPS ተሽከርካሪዎች፣ እና ማናቸውም በ MCPS ስፖንሰር የሚደረጉ የመስክ ጉዞን ጨምሮ ተማሪዎች የሚሳተፉባቸው እንቅስቃሴዎች ናቸው።

I. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ኮንትራክተሮች/MCPS Contractors ማለት ለ MCPS አገልግሎቶችን የሚሰጡ የውጭ ኮንትራክተሮች እና ሌሎች ግለሰቦች፣ የኮንትራክተሮችን ቀጥተኛ ተቀጣሪዎች ጨምሮ፣ ንኡስ ኮንትራክተሮች፣ እና/ወይም ዋናው ኮንትራክተር ከ MCPS ጋር የገባውን ኮንትራክት ለማሠራት የሚጠቀምበት የግል ኮንትራክተር/ኮንትራክተሮች ማለት ነው። በዚህ ደንብ የተቀመጡት የተወሰኑ ከስራ ተቋራጭ-ጋር-የተያያዙ ሂደቶች በMCPS ስራ ተቋራጮች ተግባራዊነታቸው ለMCPS አገልግሎቶች በሚሰጡበት ጊዜ ሲሆን እንዲሁም ማናቸውንም ህጋዊ ግዴታዎች አይወስኑም ወይም አቀይሩም።

J. ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ሲስተም አቀፍ የልጅ ጉስቁልና ጉዳይ ተጠሪ/MCPS Systemwide Child Abuse Contact– የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በቺፍ ኦቭ ስታፍ ጽ/ቤት፣ የተማሪ ደህንነት እና ሥርአት ማክበር፣ County MDT ጋር በመገናኘት ለ MCPS አማካሪ የሚሆን እና የ MCPS ሠራተኞች ለተጠርጣሪ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ምላሽ እንዲሰጡ የሚያስተባብር የመጀመሪያ ሲስተም አቀፍ ተጠሪ ሲስተም አቀፍ የልጅ ጉስቁልና ጉዳይ ተጠሪ ይሰይማል። በዚህ ደንብ የተለዩ ሃላፊነቶች ለማሟላት እንዲያግዙ የMCPS ስርአት-አቀፍ የልጅ ማጎሳቆል መገናኛ ሌሎች የሰራተኛ አባላትን እንዳስፈላጊነቱ መሰየም ይችላል።

K. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ በጎፈቃደኞች/MCPS Volunteers ወላጆች/ሞግዚቶች እና ሌሎች የቤተሰብ አባላትን፣ እና በልጆች ትምህርት ላይ ፍላጎት ኖሯቸው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ተማሪዎችን ለመደገፍ ጊዜአቸውን እና ጉልበታቸውን የሚሰጡ የማህበረሰብ አባላትን በ "MCPS Regulation IRB-RA" ድንጋጌ መሠረት የሚከናወን በጎፈቃደኞች በትምህርት ቤቶች/Volunteers in Schools ያካትታል። በዚህ ደንብ የተቀመጡት የተወሰኑ ከበጎ-ፈቃድ-ጋር-የተያያዙ ሂደቶች በMCPS በጎ-ፈቃድ ተግባራዊነታቸው ለMCPS አገልግሎቶች በሚሰጡበት ጊዜ ሲሆን እንዲሁም ማናቸውንም ህጋዊ ግዴታዎች አይወስኑም ወይም አቀይሩም።

L. ቸልተኝነት/Neglect ማለት ልጅ ወይም ተጋላጭ ጎልማሳ ሰውን በቸልታ መተው [2]ወይም ሌላ ተገቢ እንክብካቤ ወይም ጥንቃቄ ለማድረግ አለመቻል፣ ወይም ልጅ ወይም ተጋላጭ የሆነ(ች) ጎልማሳ በማንኛውም ወላጅ፣ ሞግዚት፣ ቤተሰብ ወይም የቤተሰብ አባል፣ ጎረቤት፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኛ፣ በጎፈቃደኛ ወይም ኮንትራክተር፣ በኃላፊነት ቦታ ላይ የሚገኝ ሰው፣ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ተንከባካቢ ወይም አሳዳጊነት/በጠባቂነት የሚሠራ/የምትሠራ ሰው፣ ወይም የልጅ ወይም ተጋላጭ የሆነ ጎልማሳ ከዚህ በታች በተጠቀሱ ሁኔታዎች የመቆጣጠር ኃላፊነት ያለበ(ባ)ት ሰው ትኩረት አለመስጠት/ተገቢ ያልሆነ አያያዝ፦

1. የልጁ/የልጇቱ ወይም የደካማ አዋቂ ጤንነት ወይም ደህንነት መጎዳቱ ወይም ለጉዳት አስጊ ሁኔታ ላይ መገኘቱ፣ ወይም

2. የኣእምሮ መጎዳት በልጁ/በልጇቱ ወይም በደካማ ኣዋቂ ላይ ወይም የኣእምሮ ጉዳት በከፍተኛ ኣስጊ ሁኔታ ላይ።

---

[2]በሜሪላንድ፣ ከ8 ዓመት እድሜ በታች ልጅ ቢያንስ 13 ዓመት እድሜ የሞላው/ት ለመጠበቅ የሚችል/የምትችል የሚታመን/የምትታመን ሰው በሌለበት እቤት ውስጥ፣ በትምህርት ቤት፣ ወይም በመኪና ውስጥ ብቻው(ዋ)ን መተው ክልክል ነው።

M. በት/ቤት የተመሠረቱ የልጅ ጉስቁልና ጉዳይ ሠራተኞች/School-based Child Abuse Liaisons – እያንዳንዱ ርእሰመምህር(ት) የትምህርት ቤት ካውንስለር ወይም ሌላ የሥራ ባልደረባ በት/ቤት ስለ ልጅ ጉስቁልና የሚከታተል/የምትከታተል ሠራተኛ ይመድባሉ። በት/ቤት ስለ ልጅ ጉስቁልና የሚከታተል/የምትከታተል ሠራተኛ የልጅ ጉስቁልናን እንደሚገነዘቡ፣ ሪፖርት ማድረግ እና ማጎሣቆልን እና በቸልተኝነት መተውን ስለመከላከል በትምህርት ቤት ለሚሠሩ ሠራተኞች በማሰልጠን/በማንቃት ርእሰመምህሩ(ሯ)ን ያግዛል/ታግዛለች። የተጠረጠረ ማጎሣቆል/ጥቃት/እንግልት ወይም ቸልተኝነት-ትኩረት የተነፈገ ሪፖርት ከተደረገ በኋላ፣ በትምህርት ቤት የልጅ መጎሣቆልን/እንግልት የሚከታተል/የምትከታተል ሠራተኛ ለተጠረጠረው የልጅ መቆሣቆል ጉዳይ ምላሽ በመስጠት የትምህርት ቤት ርእሰመምህርን ይረዳል/ትረዳለች እና ከካውንቲው MDT ተሣታፊዎች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች እና ለተጎጂው(ዋ) የሚደረጉ እርዳታዎችን በማስተባበር አገናኝ በመሆን ይረዳል/ትረዳለች። በትምህርት ቤት የልጅ መጎሣቆልን/እንግልት የሚከታተል/የምትከታተል ሠራተኛ ስብሰባ እንዲሳተፍ/እንድትሳተፍ ወይም ሪፖርት ላይ ለተገለጸ(ች)ው ተጎጂ ተማሪ የተባበረ አገልግሎት ለመስጠት ብቻ ወደ ካውንቲ MDT ይጋበዛል/ትጋበዛለች። በትምህርት ቤት የልጅ መጎሣቆልን/እንግልት የሚከታተል/የምትከታተል ሠራተኛ የልጅ መጎሣቆልን/እንግልት ስለመገንዘብ፣ ሪፖርት ማድረግ፣ እና መከላከልን ትኩረት ያደረገ ሙያዊ ስልጠና ይሰጠዋል/ይሰጣታል።

N. መበቀል/Retaliation ማለት አንድን ሰው ማስፈራራት ወይም ካልሆነም የመቅጣት ድርጊት ነው ስለ–

1. ተጥሷል የተባለ ህግ፣ መመርያ፣ ወይም ደንብ ማመልከት፤ ወይም

2. ተጣሰ በተባለ ምርመራ መሳተፍ።

O. ለጉዳት/ለጥቃት የተጋለጡ ጎልማሣ-አዋቂ ሰዎች/Vulnerable Adults 18 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ እድሜ ያላቸው በሪፖርት አድራጊው(ዋ) እምነት አካላዊ ወይም የአእምሮ አቅም በማጣታቸው የተነሣ ለራሳቸው በየቀኑ እንክብካቤ ለማድረግ ስለማይችሉ ጉዳት/እንግልት የሚደርስባቸው ማለት ነው።

III. ለ MCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ እና በጎ-ፈቃደኞች ዘገባ የማቅረብ ሃላፊነት

A. ሪፖርት የማቅረብ ሃላፊነት መጠን-ወሰን። ሁሉም የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ እና በጎ-ፈቃደኞች በግለሰብ ደረጃና በቀጥታ ማንኛውንም የተጠረጠረ የልጅ ወይም የደካማ አዋቂ መጎሳቆል ወይም ቸልታ ማመልከት/ዘገባ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡-

1. ተጠቂ ነው/ናት ተብሎ/ላ የሚጠረጠረው/የምትጠረጠረው በአመልካቹ/ቿ ግለሰብ ደረጃ ይታወቅም/ትታወቅም አይታወቅም/አትታወቅም።

2. ድሮ በደል እንደደረሰ ለማመን ምክንያት በሚኖርበት በማንኛውም ጊዜ፣ ምንም እንኳን አጋጣሚው ሲታወቅ/ሲገለጥ ተጠርጣሪው/ዋ ተጎጂ ትልቅ ሰው ቢሆንም/ብትሆንም።

3. ልጁ/ልጂቱ ወይም አቅመ ደካማው/ዋ አዋቂ የትም ይኑር/ትኑር እናም የተጠረጠረው በደል ወይም ቸል መባል /ተገቢውን እንክብካቤ ያለማግኘት ተፈፀመበት የተባለው ስፍራ የትም ይሁን የት።

B. የቃል ማመልከቻ/ሪፖርት። የ MCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ ወይም በጎ-ፈቃደኞች ስለተጠረጠረ መጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት በአፋጣኝ የቃል ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው።

1. የ CPS/APS ማስታወቂያ። የተጠረጠረ ማጎሳቆል ወይም ቸልታ ካለ እያንዳንዱ የ MCPS ሰራተኛ፣ የስራ ኮንትራክተር፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ የቃል ዘገባ/ማስታወቂያ መደረጉን የማረጋገጥ የግል ሃላፊነት አለበት/ባት።

a) የልጅ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት የቃል ሪፖርቶች ወድያውኑ፣ የ 24-ሰአት የቴሌፎን አገልግሎት በሚሰጠው፣ (240-777-4417) ለ CPS ሪፖርት መደረግ አለባቸው።

b) የደካማ ኣዋቂ ማንሳቆል ወይም ቸልተኝነት ሁሉም የቃል ዘገባዎች በ Montgomery County የጤናና የሰብኣዊ ኣገልግሎቶች መምርያ ውስጥ የእርጅና እና አካለ ስንክልና የመረጃና እርዳታ ክፍል (240-777-3000) ሪፖርት መደረግ ኣለባቸው።

c) ኣንድ ግለሰብ ማንሳቆልን ወይም ቸልተኝነትን ስለ ማስታወቅ ጥርጣሬ ካለው/ካላት፣ ጥርጣሬውን ለ CPS (ወይም APS ለደካማ ኣዋቂዎች) በማመልከት በኩል መሳሳት ኣለባቸው።

d) የተጠረጠረን ማንሳቆል ወይም ቸልተኝነት ዘገባ ከማቅረብ ኣስቀድሞ፣ የተጠረጠረውን ማንሳቆል ወይም ቸልተኝነት ጉዳይ ትክክለኛነት ለመወሰን ምርመራ ማካሄድ የማንም የ MCPS ሰራተኛ፣ የስራ ኮንትራክተር፣ ወይም በጎ ፈቃደኛ ሚና ኣይደለም።

e) ኣንድ ልጅ ወይም ደካማ ኣዋቂ የተጠረጠረን ማንሳቆል ወይም ቸልተኝነት በሚመለከት ለ MCPS ሰራተኛ፣ የስራ ተቋረጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ መረጃ ቢያቀርብ/ብታቀርብ፣ ያ/ያቺ ግለሰብ የተወሰኑ ተከታይ ጥያቄዎችን ጉዳዩን እና ጉዳቶችን ኣጭር መግለጫ፣ የት እንደደረሱ፣ እና ጥቃት ያደረሰ(ች)ውን ተጠርጣሪ ስምና መግለጫ ለመጠየቅ ይችላል/ትችላለች። የሆነ ሆኖ ሪፖርት ከመደረጉ በፊት፣ የ MCPS ሰራተኞች፣ የስራ ኮንትራክተር፣ ወይም በጎ-ፈቃደኞች ከተደጋገመ፣ ዝርዝር ቃለ-መጠይቅ ተፈላጊ ያልሆነ ኣሰቃቂ የኣእምሮ ሁኔታ እንዳያስከትል ከማንኛውም ተጠቂ ወይም ምስክር ከተባለ/ች ጥያቄና መልስ ወይም የፅሁፍ መግለጫ መጠየቅ የለባቸውም።

f) ሪፖርት ከመደረጉ በፊት፣ የ MCPS ሰራተኞች፣ የስራ ኮንትራክተሮች፣ ወይም በጎ-ፈቃደኞች ተጠርጣሪ ኣጥቂዎች ጋር ቃለ መጠይቅ ማድረግ ወይም ስለ ድርጊቱ ከነሱ ጋር መወያየት የለባቸውም።

g) ማንሳቆልን ወይም ቸልተኝነትን ለመጠርጠር በቂ ምክንያት መኖሩን እያወቁ ደብዛ ለማጥፋት የሚሞክሩ የ MCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ ወይም በጎ-ፈቃደኞች የተጠረጠረ መንሳቀልን ወይም ቸልተኝነትን እንዲከዱ ተማሪዎች ላይ ተፅእኖ ማድረግ የለባቸውም።

2. የርእሰ መምህር/የበላይ ተቆጣጣሪ ማስታወቂያ። ለCPS (ወይም ለAPS ለደካማ ኣዋቂዎች) የቃል ዘገባ ከተደረገ በኋላ፣ የ MCPS ሰራተኛ፣ የስራ ኮንትራክተር፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ፣ ሪፖርት አቅራቢ ግለሰብ በት/ቤት የሚገኝ/የምትገኝ ከሆነ፣ ለርእሰመምህሩ/ሯ ወድያውኑ ማስታወቅ አለበ(ባ)ት። ዘገባ ኣቅራቢው/ዋ በት/ቤት-የተመሰረተ/ች ካልሆነ፣ ለሚሰሩበት የ MCPS ፅ/ቤት የበላይ ተቆጣጣሪን፣ እንዲሁም ልጁ/ልጇቱ ወይም ደካማ አዋቂው/ዋ ለሚከታተለው ት/ቤት ርእሰመምህር፣ ያስታውቃል/ታስታውቃለች። CPS ወይም APS ለአመልካቹ(ቿ)/ለዘጋቢው(ዋ) ምርመራውን እየተወ(ች)ው ወይም ምርመራዉን በመለየት/በማጣራት ላይ መሆኑን ቢነግርም/ብትነግርም ማስታወቂያው የግድ መስጠት አለበት።

a) ማስታወቂያ እንደተደረገ፣ ርእሰመምህሩ/ሯ ወይም ቀጥተኛ ተቆጣጣሪ ከዚህ በታች በክፍል IV እንደተቀመጠው ተከታይ ቅደም-ተከተሎችን ይጀምራል/ትጀምራለች፣ እናም እታች በክፍል III(B)(3)(c) በተገለጹት ሁኔታዎች መሰረት የ MCPD ን የልዩ ተጠቂዎች ምርመራዎች ክፍልን ይገናኛሉ።

b) ለCPS (ወይም APS ለደካማ ኣዋቂዎች) ሪፖርቱ ኣንዴ ከቀረበ በኋላ፣ በክፍል IV ከተገለጸው በስተቀር ርእሰመምህሩ/ሯ ወይም ማንኛውም ሌሎች የMCPS ሰራተኞች ማንኛቸውንም የውስጥ ምርምራ ማካሄድ የለባቸውም።

c) ርእሰመምህሩ/ሯ ወይም ቀጥተኛ ተቆጣጣሪ የቃል ሪፖርት እላይ በክፍል III(B)(1) በተገለፀው መሰረት መደረጉን እና የፅሁፍ ሪፖርት በክፍል III(C) ታች በተገለፀው መሰረት ገቢ መደረጉን ማረጋገጥ አለባቸው።

d) ይህ ደንብ ለርእሰመምህር ወይም ለተቆጣጣሪ ማስታወቅ የሚጠይቅ ቢሆንም፣ ማስታወቂያው የMCPS ሰራተኞች፣ የስራ ኮንትራክተሮች፣ ወይም በጎ-ፈቃደኞች፣ የሪፖርት ግዴታዎችን አያሟላም። እላይ እንደተገለፀው፣ ለCPS (ወይም APS ለዳካማ አዋቂዎች) በግለሰብ ደረጃና በቀጥታ ማመልከትም በተጨማሪ ይፈለግባቸዋል።

e) የ MCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ የት/ቤት ርእሰመምህርን ወይም ቀጥተኛ የበላይ ተቆጣጣሪን ስለ ማሳወቅ ቅሬታ በሚኖርበት ወቅቶች፣ ሪፖርት አቅራቢው/ዋ በምትኩ/ኳ ለ MCPS ስርኣት-አቀፍ የልጅ ማጎሳቆል ጉዳዮችን ለሚከታተል ኃላፊ ማሳወቅ ይቻላል።

3. የ MCPD ማስታወቂያ። ሪፖርቶችን መከታተል ለማቃለልና ለማስተካከል፣ MCPS እና የካውንቲ MDT አባሎች ከ MCPS ሰራተኛ፣ የስራ ኮንትራክተር፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ ለሚቀርቡ የቃል ሪፖርቶች ተቀዳሚ ወኪል ድርጅቶች መሆን ያለባቸው CPS ወይም APS (የደካማ/ተጋላጭ አዋቂዎችን ጉዳይ የሚከታተል ቢሮ) መሆን እንዳለባቸው ተስማምተዋል። በተጨማሪ የ MCPD የልዩ ተጠቂዎች ምርመራ ክፍል ከዚህ በታች በተቀመጠው መሰረት ስለተጠረጠረ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ይነገራል ወይም ወድያውኑ እንዲያውቀው ይደረጋል፡-

a) CPS (ወይም APS ለደካማ አዋቂዎች) የማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ሁኔታ የሚያካትት የቃል ሪፖርት ሲደርሰው፣ CPS (ወይም APS ለደካማ አዋቂዎች) የMCPD የልዩ ተጠቂዎች ምርመራዎች ክፍል ጋር በቅርብ እንደሚማካከር MCPS ይገነዘባል።

b) በእነርሱ ስር ያለ ማንኛውም የMCPS ሰራተኛ፣ የስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ በግለሰብ ደረጃና በቀጥታ ለ CPS (ወይም APS ለደካማ/ለተጠቂ አዋቂዎች) ሪፖርት ማቅረቡ(ቧ)ን ከማረጋገጥ በተጫማሪ፣ ርእሰመምህራን እና ተቆጣጣሪዎች የተጠረጠረ ፆታዊ ጥቃት በክፍል II(A)(2) እላይ ፍች እንደተሰጠው፣ ወይም አዋቂ ተጠቂን የሚያካትት የፆታ ጥቃት የተጠረጠረ ማጎሳቆል ሪፖርት ከተቀበሉ ወድያውኑ ለ MCPD የልዩ ተጠቂዎች ምርመራ ክፍል ያስታውቃሉ።

c) ለሌሎች የማጎስቆል ወይም ቸልተኝነት ጥርጣሬ ምላሽ ለመስጠት፣ MCPS ከ MCPD የልዩ ተጠቂዎች ምርመራዎች ክፍል እርዳታ ሊጠይቅ ይችላል እና፣ በሁሉም አስቸኳይ ሁኔታዎች፣ የ MCPS ሰራተኞች፣ የስራ ተቋራጮች፣ ወይም በጎ-ፈቃደኞች የህዝብ ደህንነት ማገናኛ ማእከል (911) ወይም 301-279-8000 መደወል አለባቸው። MCPD በጉዳዩ ቢካተትም ባይካተትም፣ የ MCPS ሰራተኞች፣ የስራ ተቋራጮች፣ ወይም በጎ-ፈቃደኞች እላይ እንደተገለፀው በግልና በቀጥታ አስቸኳይ ሪፖርት ለ CPS (ወይም APS ለደካማ/ተጋላጭ አዋቂዎች) የማመልከት ግዴታቸውን አሁንም ማሟላት አለባቸው።

C. የፅሁፍ ሪፖርት። የማጎሳቆል ወይም የቸልተኝነት የቃል ሪፖርት የሚያደርገው/የምታደርገው ግለሰብ በ MCPS ፎርም 335-44፣ የተጠረጠረ የልጅ ማጎሳቆልና ቸልተኝነት ሪፖርት ላይ ለ CPS (ወይም APS ለደካማ/ተጋላጭ አዋቂዎች) የፅሁፍ ሪፖርት ማቅረብ አለበ(ባ)ት።

1. የፅሁፍ ሪፖርቱ ለ CPS (ወይም APS ለደካማ/ተጋላጭ አዋቂዎች) የተጠረረ ማጎሳቆል እና/ወይም ቸልተኝነት መኖሩን ከተጋለጠ በኋላ በ48 ሰኣት ውስጥ መቅረብ አለበት ምንም እንኳን CPS፣ APS፣ እና/ወይም MCPD ምርመራውን መቀጠል የተተወ ወይም ፋይሉን እየተዘጋ መሆኑን ለሪፖርት አቅራቢው(ዋ) የተገለጸ ቢሆንም፣ የፅሁፍ ሪፖርቱ የግድ መደረግ አለበት።

2. ከ 2019-2020 የትምህርት ዓመት ጀምሮ፣ የ MCPS ሠራተኞች እና ሌሎችም፣ እንደአስፈላጊነቱ፣ ከአውታረ-መረብ ኤሌክትሮኒክ ፖርታል ድረ-ገጽ ጋር የተገናኘ የጽሑፍ ሪፖርቶችን እንዲያቀርቡ እናበረታታለን። ይህም ማለት ከዚህ በታች ለሚገኙት የሚመለከታቸው ጽ/ቤቶች እና ኤጀንሲዎች ወዲያዉን ቅጅዎችን ያስተላልፋል ማለት ነው። አማራጭ የሆነውን በወረቀት ከተገለገሉ፣ የሪፖርቱ ቅጅዎች ልሙጥ በሆነ ኤንቨሎፕ፣ ታሽጎ፣ አድራሻ፣ እና ሚስጥር የሚል ምልክት ተጽፎበት መሠራጨት አለበት። ኤንቬሎፑ በተለመደው የቢሮ ፖስታ መላላኪያ መከተት አለበት። ርእሰመምህር ወይም የቅርብ ሱፐርቫይዘር ቅጂዎቹ በ MCPS Form 335-44 ላይ በተገለጸው መሠረት የተላኩ መሆኑን ያረጋግጣሉ ለ–

   a) MCPS ስርኣት-ኣቀፍ የልጅ መጎሳቆል ጉዳይ ኣገናኝ መኮንን፣ ቅጅዎችን በምስጢራዊ ማህደር የሚንከባከብ፤

   b) የ MCPD የልዩ ተጠቂዎች ምርመራዎች ክፍል፤ እና

   b) Montgomery County ስቴት የኣቃቤ ህግ ፅ/ቤት።

3. ርእሰመምህራን እና ተቆጣጣሪዎች ማናቸውንም የሪፖርት ቅጂዎችን ኣይዙም፣ ነገር ግን የሚከተሉትን ብቻ የሚያካትቱ የሁሉንም የተዘገቡ ጉዳዮች ምስጢራዊ ማስታወሻ ደብተር ብቻ ይይዛሉ –

   a) የልጅ ወይም የደካማ/ተጋላጭ ኣዋቂ ስም፣

   b) የተጠርጣሪው(ዋ) ስም፣ ከታወቀ/ች፣

   c) የቃል ሪፖርት የቀረበበት ቀንና ሰኣት፣

   d) ሪፖርት የቀረበለት የሰራተኛ ኣባል እና ወኪል ድርጅት ስም፤ እና

   e) ቅጹ በፖስታ የተላከበት ወይም በኤሌክትሮኒክ የቀረበበት ቀን።

## IV. ጥርጣሬዎች ሪፖርት ከተደረጉ በኋላ ተከታታይ ሃላፊነቶች

### A. ምርመራዎች

1. ሁሉም የMCPS ሰራተኞች፣ የስራ ተቋራጮች፣ እና በጎ-ፈቃደኞች ከካውንቲ MDT ተሳታፊ ወኪል ድርጅቶች እና ሌሎች የውጭ ወኪል ድርጅቶች ጋር በተጠረጠሩ የማጎሳቆልና ቸልተኝነት ምርመራዎች ሙሉ በሙሉ ይተባበራሉ። የወኪል ድርጅቶችን ምርመራዎች በሚመለከት መረጃ የመጋራት የጊዜ ቅደም ተከተሎች በ MCPS እና በካውንቲው MDT ኣባሎች መካከል በተደረገው ስምምነት/Memorandum of Understanding ውስጥ ተገልጸዋል። የካውንቲ MDT ተሳታፊ ወኪል ድርጅቶች ምርመራዎቻቸውን ወቅት እየጠበቁ እና የመማርያ ክፍልንና የት/ቤት ማህበረሰብ ረብሻን በመቀነስ ለማከናወን ተስማምተዋል።

2. በኣንድ የማጎሳቆል ወይም የቸልተኝነት ምርመራ ወቅት CPS፣ APS፣ ወይም MCPD ኣንድን ተማሪ በ MCPS ንብረት ላይ በትምህርት ሰኣት ሊጠይቁ(ቋ)ት ይችላሉ። በሜሪላንድ ኮድ ደንቦች (COMAR) 13A.08.01.13 መሰረት፣ ርእሰመምህሩ/ሯ በቃላመጠይቁ ወቅት ኣንድ የት/ቤት ባለስልጣን ይኑር ኣይኑር ይወስናል/ትወስናለች። ውሳኔ ኣወሳሰድ ላይ ርእሰመምህሩ/ሯ ከ CPS፣ APS፣ ወይም ከ MCPD ተወካዮች ጋር የመካከራል/ትመካከራለች። የት/ቤት ባለስልጣን መመረጥ ኣለበት፣ ከሚጠየቀው ተማሪ ኣስተያየት ተጨምሮበት፣ ኣንድ-በኣንድ መሰረት ለተማሪው/ዋ ድጋፍና መፅናኛ ለመስጠት። የወላጆች/ኣሳዳጊዎች ማስታወቅ ሁኔታ እታች በክፍል IV.D. ይታያል።

4. MCPS ሰራተኞች፣ የስራ ኮንትራክተር፣ እና በጎ-ፈቃደኞች በ CPS፣ APS፣ MCPD፣ ወይም በሌላ የውጭ ወኪል ድርጅት ስለተጠረጠረ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት በእንጥልጥል ላይ የሚገኝ ምርመራ ላይ ተፅእኖ ሊያስከትል የሚችል ማንኛውንም እርምጃ መውሰድ የለባቸውም። ከመርማሪ ወኪል ድርጅቶች በቅድሚያ ፈቃድ ሳይገኝ MCPS በዳይ የተባለ(ች)ውን የተጠረጠረ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ሪፖርት መቅረቡን ኣይነግረውም/ኣይነግራትም።

B. የማጎሳቆል ወይም የቸልተኝነት ተግባር በ MCPS ንብረት ላይ እና/ወይም የ MCPS ሰራተኞችን፣ የስራ ኮንትራክተሮችን፣ ወይም በጎ-ፈቃደኞችን የሚያካትቱ ጥርጣሪዎች ኣያያዝ ተጨማሪ ቅደም-ተከተሎች

1. ክትትል በርእሰመምህር/ት ወይም ቀጥተኛ ተቆጣጣሪ

የተጠረጠረ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት በ MCPS ንብረት ላይ ወይም በ MCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ ተከናወነ የሚባል ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት የሚያካትት የሚመለከት ለCPS (ወይም APS ለደካማ ኣዋቂዎች) የተደረገ የቃል ሪፖርት ማስታውቂያ ከተቀበሉ በኋላ ወዲያዉ ርእሰመምህር ወይም ቀጥተኛ ተቆጣጣሪ የሚከተሉትን እርምጃዎች ይወስዳሉ፡-

a) የቃል ሪፖርት ለ CPS የቀረበ መሆኑን (ወይም ተጋላጭነት ስላላቸው ኣዋቂ ሰዎች - ለ APS) እና ከላይ Section III ላይ በተገለጸው መሠረት ከዚያ በኋላ የጽሑፍ ሪፖርት በ 48 ሠዓት ውስጥ መቅረቡን ማረጋገጥ

b) የጾታዊ ጥቃት ጥርጣሬን በሚመለከት ከላይ "Section III" ላይ በተገለጸው መሠረት ለ፡- Special Victims Investigations Division of MCPD ያሳውቁ

c) ከ Office of School Support and Improvement (OSSI) እና ከ MCPS ተቋም አቀፍ ስለልጅ ጉስቁልና የሚመለከተውን ክፍል ወይም ተወካይ ጋር ይነጋገሩ

d) ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ተቋም አቀፍ የልጅ ማጎሳቆል ግንኙነት እና የካውንቲ MDT/"MCPS Systemwide Child Abuse Contact and County MDT" ተሳታፊ ኤጀንሲዎች፣ ተጠርጣሪ በተጠርጣሪ ተጋላጭ እና ሌላ ተማሪ ላይ ጥቃት አድራጊው(ዋ) በፍጥነት ጥቃት እንደማያ(ታ)ደርስ እርግጠኛ መሆን።

e) ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ተቋም አቀፍ የልጅ ማጎሳቆል ግንኙነት እና የካውንቲ MDT/"MCPS Systemwide Child Abuse Contact and County MDT" ተሳታፊ ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር ጥቃት ለደረሰባቸው ተማሪዎች ቤተሰቦች/ሞግዚቶች በ Section IV(D) ከዚህ በታች በተገለጸው መሠረት በፍጥነት ለማሳወቅ የሚያስችል እቅድ/ፕላን ለማዘጋጀት እና ለሌሎች የማህበረሰብ አባላት ጭምር ማሳወቅ ያስፈልግ እንደሆነ ለመወሰን እና ከዚህ በታች በ Section IV(E) ላይ እንደተገለጸው እቅድ/ፕላን ማዘጋጀት።

2. ክትትል በ MCPS ስርኣት-አቀፍ የልጅ መጎሳቆል ጉዳይ የሚመለከተው አገናኝ መኮንን/የሚመለከተዉ

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ንብረት (MCPS) ውስጥ በ MCPS ሠራተኛ፣ ኮንትራክተር፣ ወይም በጎፈቃደኛ፣ አማካይነት ተከስቷል ተብሎ የሚጠረጠር ማጎሣቆል ወይም በቸልተኝነት/በግድየሌሽነት የመተው ሪፖርት ሲደርስ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የተቋም አቀፍ የልጅ ማጎሣቆል ግንኙነት ተጠሪ/MCPS Systemwide Child Abuse Contact will –

a) ከ CPS፣ MCPD፣ እና ሌላ የካውንቲው MDT ተሣታፊ ኤጀንሲዎች ጋር በአግባቡ ግንኙነት መደረጉን ያረጋግጣል፣

b) ተጠርጣሪው/ዋ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኛ፣ ኮንትራክተር፣ ወይም በጎፈቃደኛ ከሆነ/ች ወደ "Office of Employee Engagement and Labor Relations (OEELR)" መገናኘት፣ እና

c) ሌሎች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞችን በማስተባበር ከ OEELR የ MCPS ተወካዮችን ጭምር፣ Office of Student and Family Support and Engagement፣ OSSI፣ Office of the General Counsel፣ Department of School Safety and Security፣ እና Department of Communications፣ ስለ ሁኔታው ምላሽ ስለመስጠት ከርእሰመምህር ወይም የቅርብ ሱፐርቫይዘር ጋር በተከታታይ መምከር እና አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት።

3. በ OEELR አማካይነት የሚደረግ ክትትል

ጥቃት የፈጸመው/የፈጸመችው ተጠርጣሪ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኛ፣ ኮንትራክተር፣ ወይም በጎፈቃደኛ ከሆነ(ች)፣ OEELR –

a) የክስ ፋይል ይከፍታል፣

b) ስለተጠርጣሪው(ዋ) ጠቃሚ መረጃዎችን ለማግኘት የሠራተኛ ፋይል ይመረምራሉ፣ እና

c) ከርእሰመምህር/ሱፐርቫይዘር፣ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የልጅ ጉስቁልና ተጠሪ/MCPS Systemwide Child Abuse Contact፣ እና ከካውንቲው MDT ኤጋር ኤጀንሲዎች ጋር በመነጋገር ማናቸውም ምርመራ እየተካሄደ ባለበት ወቅት ተጠርጣሪው(ዋ) ወደ ተማሪው(ዋ) እንዳይደርስ/እንዳትደርስ ማቀብ ወይም አስተዳደራዊ እረፍት ላይ የማቆየት እርምጃ መውሰድ።

(1) OEELR የMCPSን ሰራተኛ የአስተዳደር ፈቃድ ላይ ያደርገዋል/ያደርጋታል፣ ሌላ እርምጃ እንዲወሰድ የሚያስገድድ ትርጉም ያዘለ፣የሚያሳምን መረጃ ካለ በስተቀር።

(2) አጥቂ ነው የተባለው የስራ ተቋራጭ ከሆነ፣ ኣቅራቢውን ለማሳወቅ እና በማንሳቆል ወይም ቸልተኝነት የተጠረጠረ(ች)ውን ግለሰብ ኣገልግሎቶቹን ምርመራው እስኪያልቅ ድረስ ለማቋረጥ፣ ሌላ እርምጃ እንዲወሰድ የሚያስገድድ ትርጉም ያዘለ፣የሚያሳምን መረጃ ካለ በስተቀር፣ OEELR በOffice of the Chief Operating Officer/በዋናው የስራ መኮንን ፅ/ቤት (OCOO) ከሌሎች ሰራተኞች ጋር ኣብሮ ይሰራል/ትሰራለች።

(3) እጥቂ ነው የተባለ(ች)ው በጎ-ፈቃደኛ ከሆነ(ች)፣ ምርመራው እስኪያልቅ ድረስ ግለሰቡ/ቧ በMCPS ንብረት ላይ ወይም MCPS ስፖንሰር ባደረጋቸው እንቅስቃሴዎች በጎ-ፈቃድኛነቱን ለመወሰን፣ ሌላ እርምጃ እንዲወሰድ የሚያስገድድ ትርጉም ያዘለ፣የሚያሳምን መረጃ ካለ በስተቀር፣ OEELR ከ OSSI እና ከ OCOO አብሮ ይሰራል/ትሰራለች።

(4) ይህን ፐላን በመተግበር ላይ፣ ኣጥቂ የተባለ(ች)ው ለአስተዳደራዊ ፈቃድ፣ ኣገልግሎቶችን ማቋረጥ፣ ወይም ከበጎፈቃደኝነት ልዩ ጥቅሞች መታገድ፣ ኣስፈላጊ የሆኑ ዝርዝሮችን ብቻ እንዲያውቅ/እንድታውቅ መደረጉን ለማረጋገጥ ጥንቃቄ መደረግ ኣለበት። የ MCPS የሰራተኛ ኣባሎች፣ የምርመራው ሃቀኛነት ከመበከል ለመቆጠብ፣ በቅድሚያ ከመርማሪ ወኪል ድርጅቶች ፈቃድ ሳይገኝ፣ በማንሳቆል ወይም ቸልተኝነት ጥርጣሬዎች ከተጠርጣሪ ኣጥቂ ጋር ኣይወያዩም።

d) ተከታይ የ MCPS ምርመራ። በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኛ፣ ኮንትራክተር፣ ወይም በጎፈቃደኛ፣ አግባብነት ተፈጸመ ተብሎ የሚታሰብ ማናቸውም የሚጠረጠር የማጎሳቆል ወይም ቸል የማለት ጉዳይን OEELR ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትምህርት ቦርድ Montgomery County Board of Education (Board) ፖሊሲዎች እና ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦች፣ እና/ወይም ሌላ መመሪያ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ሠራተኛ ስነምግባር ኮድ/MCPS Employee Code of Conduct ጨምሮ ከነዚህ ጋር የተጣጣመ የውስጥ ምርመራ/ግምገማ በማካሄድ፣ ተገቢ የሆነ የዲስፕሊን እርምጃ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል። CPS፣ APS፣ እና MCPD በማጣራት ላይ እያሉ ወይም ምንም አይነት እርምጃ ሳይወሰድ ጉዳዩን ዘግተውት ቢሆን እና/ወይም እንደዚህ አይነት ጉዳዮች የቦርድ ፖሊሲን፣ የ MCPS ደንቦችን፣ ኮንትራቶችን፣ እና/ወይም ሌላ መመሪያዎችን የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ሠራተኛ የስነምግባር ኮድ/MCPS Employee Code of Conduct ን ጨምሮ እነዚህን ይፃረራል በማለት የስቴት ዓቃቤ ህግ የወንጀል ድርጊት ክስ ለመመስረት ፈቃደኛ ባይሆን እንኳ OEELR የውስጥ ግምገማ/ምርመራ ያካሄዳል።

(1) በCPS፣ APS፣ MCPD እና በሌላ የውጭ ወኪል ድርጅት ምርመራ በእንጥልጥል ላይ እያለ፣ ከመርማሪ ወኪል ድርጅች በቅድሚያ ስምምነት ሳይገኝ፣ ወይም በነሱ የቀረቡ ማናቸውም ገደቦች ሁኔታ ሳይታይ፣ MCPS ከምስክሮች፣ ተጠቂ ከሚባሉ፣ ወይም የተጠረጠሩ በደለኞች ጋር ቃለ መጠይቅ ኣያካሄድም። በተጨማሪ፣ MCPS የውስጥ ምርመራዎችን ማካሄድ ያለበት ምርመራ በማካሄድ ላይ ከሚገኙት የውጭ ወኪል ድርጅቶች ሙሉ በሙሉ በመተባበር መንፈስ እና የውጩ ምርመራ ላይ ጣልቃ የማይገባ ወይም አደጋ ላይ የማይጥል መሆን አለበት።

(2) ህግ እስከፈቀደ ድረስ፣ ተጠቂ የተባሉትንና የምስክሮችን ድግግሞሽ ቃለመጠይቅ ለማስቀረት፣ የMCPS ምርመራ በፖሊስ ዘገባዎች፣ ኣረፍተሃሳቦች፣ እና በበሜሪላንድ ኣኖቴትድ ኮድ Human Services Article, Section 1-202, to avoid repetitive questioning of alleged victims and witnesses መሰረት ከካውንቲ MDT ተሳታፊ ወኪል ድርጅቶች ዘገባዎች ከተገኙ ሌሎች መረጃዎች መጠቀም ኣለበት።

(3) የMCPS ምርመራ ተቀዳሚ ኣላማ በMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ እና በጎ-ፈቃደኛ የመጥፎ ስነምግባር መረጃ መኖር ኣለመኖሩን ለመወሰን ነው። በተጨማሪ፣ ምርመራው ህግን፣ የቦርድ ፖሊሲን፣ የ MCPS ደንቦችን፣ ኮንትራቶችን፣ እና/ወይም ሌላ መመሪያ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የሠራተኛ ስነምግባር ኮድ/MCPS Employee Code of Conduct ን ጨምሮ ሌላ መመሪያዎችን በመከተል ጉዳዩ ሪፖርት መደረጉን፣ እና ተጨማሪ ሙያዊ እውቀት/professional development ወይም ሌላ የሂደት ማሻሻያ ያስፈልግ እንደሆነ ለመወሰን ነዉ።

(4) ምርመራው ከቦርድ ፖሊሲ ጋር፣ ከ MCPS ደንቦች፣ ኮንትራቶች፣ እና/ወይም ሌላ መመሪያዎች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የሠራተኛ ስነምግባር ኮድ/MCPS Employee Code of Conduct ጭምር መጣጣም ያለበት ሲሆን፣ ስለ MCPS ሠራተኞች መብት ሂደቶች፣ እና ሠራተኛው ስለ ምርመራው ውጤት እንዲያውቅ/እንድታውቅ መደረግ አለበት።

(5) የምርመራው ውጤቶች፣ ግለሰቡ/ቧ ለ MCPS ኣገልግሎቶች እስከሰጠ ድረስ እና ለኣምስት ኣመቶች ከዚያም በኋላ፣ በOEELR ምስጢራዊ የምርመራ ማህደሮች ውስጥ ይያዛሉ። ከዚያም ማህደሮቹ በቋሚ መጋዘን ይቀመጣሉ።

C. የተማሪ ድጋፍ አገልግሎቶች

1. አንድ/ዷት በተጠረጠረ/ች ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት የተካተተ/ች ልጅ ወይም ደካማ አዋቂ አስቸኳይ ህክምና ወይም የአእምሮ ጤንነት ህክምና ካስፈለገው/ጋት፣ ርእሰመምህርሩ/ሯ ወይም የርእሰምምህር ተወካይ ልጁ/ጂቱ ወድያውኑ ወደ ሆስፒታል ወይም ወደ ሌላ መገልገያ ከተገቢ አዋቂ ቁጥጥር ጋር እንዲ(ድት)ወሰድ ያደርጋል/ታደርጋለች። የ CPS (ወይም APS ለደካማ አዋቂዎች) ተወካይ በቅድሚያ ወይም በተቻለ ወድያውኑ ከዚያ በኋላ እንዲያውቅ መደረግ አለበት። በሁሉም ሌሎች አስቸኳይ ላልሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ፣ MCPS ለልጁ/ጇቱ ወይም ደካማ አዋቂ ህክምና ወይም የአእምሮ ጤንነት ህክምናን በሚመለከት ከCPS (ወይም APS ለደካማ አዋቂዎች) ተወካይ፣ ወይም ከMCPD የልዩ ተጠቂዎች ምርመራዎች ክፍል ጋር ይመካከራል።

2. በትምህርት ቤት የሚገኝ የልጅ ጉስቁልናን የመከታተል ኃላፊነት ያለው/ያላት ሰው የትምህርት ቤት ካውንስለሮች፣ የትምህርት ቤት ሳይኮሎጂስቶች፣ የተማሪ ሠራተኛ፣ እና ሌላ ተገቢ የ MCPS ሠራተኛ፣ እንዲሁም የትምህርት ቤት ነርሶች፣ የጥቃት ወይም ቸልተኝነት ተጠርጣሪ ሪፖርት ለሚያደርጉ ተማሪዎች ድጋፍ እና ምክር/ካውንስሊንግ ለመስጠት መገኘት እንዲችሉ ያመቻቻል/ታመቻቻለች።

3. የማጎሳቆል ወይም የቸልተኝነት ተጠቂ ለሆነ/ች፣ እንዲሁም ማጎሳቆልና ቸልተኝነት ለሚያስታውቁ ተማሪዎች፣ አገልግሎቶች ለማቀነባበር፣ የMCPS ስርአት-አቀፍ የልጅ መጎሳቆል አገናኝ መኮንን ከካውንቲ MDT ተሳታፊ ወኪል ድርጅቶች፣ የ MCPSን ፔሮሶኔል እና ተማሪዎችን ምስጢራዊነት የሚጠብቁ እና ያልተፈቀደ የዘገባዎች መጋለጥ እና ማጎስቆልና ቸልተኝነትን የሚመለከቱ ዘገባዎችን የሚከለክሉ ህጎች እስከፈቀዱ ድረስ ሊመካከር/ልትመካከር ይችላል/ትችላለች። ሌሎች የMCPS የሰራተኛ አባሎች በካውንቲ MDT ስብሰባዎች ወይም ምክክሮች በMCPS እና በሌሎች የካውንቲ MDT ወኪል ድርጅቶች ጋር በተመሰረቱ ቅደም-ተከተሎች መሰረት መሳተፍ ይችላሉ።

4. አንድ ርእሰምምህር አንድ የመጎሳቆል ወይም የቸልተኝነት ምርመራ አርእስት የሆነ/ች ተማሪ ምርመራ ከተጀመረ በሶስት ወሮች ውስጥ ከአካባቢ ት/ቤቱ/ቷ ራሱ(ሷ)ን ካገለለ/ች እና/ወይም ከወጣ/ች፣ ርእሰምምህሩ/ሯ የMCPS ስርአት-አቀፍ የልጅ መጎሳቆል ጉዳይ አገናኝ መኮንንን ማስታወቅ አለበ(ባ)ት፣ እሱም/እርሷም፣ በተራው/ዋ፣ ከካውንቲ MDT ወኪል ድርጅቶች ጋር እንደ አግባቡ ይመካከራል/ትመካከራለች።

D. የተማሪ ተጠቂዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ማስታወቅ

1. ርእሰመምህራን፣ በተጠረጠረ መጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ሁኔታ የተካተቱ ተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎችን ማን እንደሚያሳውቃቸው እና ያ ማስታወቂያ መቼ እንደሚሆን ለመወሰን ከMCPS ስርአት-አቀፍ የልጅ መጎሳቆል ጉዳይ አገናኝ መኮንን እና ከCPS፣ APS (ለደካማ አዋቂዎች)፣ እና/ወይም ከMCPD የልዩ ተጠቂዎች ምርመራዎች ክፍል ጋር ይተባበራሉ። MCPS ተደረገ በሚባል ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ሁኔታ የተካተቱ ተማሪዎች ወላጆ/አሳዳጊዎችን የማስታወቅ ሃላፊነት የለውም፡- (a) አጥቂ የተባለ(ች)ው የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ ያልሆነ(ች)በት፣ እና የተባለው ማጎሳቆል በMCPS ንብረት ላይ ያልሆነበት ጉዳዮች፤ ወይም (b) በርእሰምምህሩ/ሯ እና በCPS፣ በAPS (ለደካማ/ተጋላጭ አዋቂዎች)፣ እና በ MCPD የልዩ ተጠቂዎች ምርመራዎች ክፍል ግምት፣ ወላጆች/አሳዳጊዎችን ማስታወቅ ለተማሪው/ዋ ደህንነት ስጋት ሊፈጥር የሚችል (ለምሳሌ እንድ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም የቤተሰብ ወይም የመኖርያ ቤት አባል ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ፈፅሟል ተብሎ የተጠየቀ) ወይም በቆይታ ላይ ያለ ምርመራን የሚያደናቅፉ ጉዳዮች። ማስታወቅ የ MCPS ሃላፊነት ባልሆነባቸው ጉዳዮች፣ CPS፣ በAPS (ለደካማ/ተጋላጭ አዋቂዎች)፣ ወይም የMCPD የልዩ ተጠቂዎች ምርመራዎች ክፍል ወላጆች/አሳዳጊዎችን ለማስታወቅ ሃላፊዎች ናቸው።

2. ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር ግንኙነት ለማቃለል ከተፈለገ MCPS ምስጢራዊ የትርጉም አገለግሎቶች ያቀርባል።

3. ተከታዩ ካልሆነ በስተቀር ያለ ወላጅ ፈቃድ/ስምምነት አንድ ተማሪ ለጥያቄ ወይም ለሜዲካል ምርመራ ከትምህርት ቤት ግቢ መወገድ አይኖርበ(ባ)ትም –

   a) Montgomery County የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምርያ ልጁ(ጂቱ)ን ለማንሳት የጠባቂ ወይም የመጠለያ እንክብካቤ ስልጣን ካለው፤ ወይም

   b) ተማሪው/ዋ አስቸኳይ ህክምና ካስፈለገው/ጋት።

4. ኣንድ/ዲት ተማሪ ሲ(ስት)ወገድ፣ ርእሰመምህሩ/ሯ የመወገዱን ማስታወቂያ ለወላጆች/አሳዳጊዎች ወድያው መደረጉን ያረጋግጣል/ታረጋግጣለች። በጋራ ስምምነት፣ የዚህ ኣይነቱ ማስታወቂያ፣ ጉዳይ በጉዳይ መሰረት፣ ለCPS፣ APS (ለደካማ ኣዋቂዎች)፣ ወይም ለMCPD የልዩ ተጠቂዎች ምርመራዎች ክፍል መተላለፍ ይችላል።

E. ለሌሎች በት/ቤት ማህበረሰብ ውስጥ ማስታወቅ

ርእሰ መምህሩ(ሯ) ከ MCPS Systemwide Child Abuse Contact፣ OSSI፣ MCPS Department of Communications፣ እና ከካውንቲው MDT ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር ሌሎች የትምህርት ቤት ማህበረሰብ እንዲያውቁት መድረግ እንዳለበት ለመወሰን እና የጊዜ ሠሌዳን የሚገልጽ እቅድ ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች።

   a) ማናችውም ምርመራ እየተካሄደ ባለበት ወቅት እና ከእስራት ወይም ክስ ከመመስረቱ አስቀድሞ፣ ርእሰመምህሩ(ሯ) ከ MCPS Systemwide Child Abuse Contact፣ MCPS Department of Communications፣ እና የካውንቲው MDT ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር በሚከተሉት ምክንያቶች ለሌሎች የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ማሳወቅ እንደሚያስፈልግ ካልተወሰነ በስተቀር –

      (1) ለተጠቂ ወገን የላቀ ጥቅም የሚያተርፍ ከሆነ፤

      (2) በመካሄድ ላይ በሚገኝ ምርመራ ጣልቃ የማይገባ ከሆነ፤ ወይም

      (3) በሜሪላንድ ህግ የተከለከለ ማንሳቀል ወይም ቸልተኝነት የሚመለከት ያልተፈቀደ የመዛግብት ወይም ዘገባዎች መጋለጥ የማይጠይቅ ከሆነ።

   b) ለእስር የሚዳርግ ወይም የሚያስከሥስ የተጠረጠረ ጥቃት ወይም የቸልተኝነት ጥፋት ሁኔታ የተከሰተዉ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ውስጥ ከሆነ ወይም ተጠርጣሪው(ዋ) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኛ፣ ኮንትራክተር፣ ወይም በጎፈቃደኛ ከሆነ(ች) MCPD በተቻለ መጠን በቅድሚያ ለ MCPS ለማሳወቅ ተስማምቷል። ቁጥጥር ስር ማዋልን ከት/ቤት ንብረት ርቀው እና ከትምህርት ሰኣቶች ውጭ፣ በተቻለ መጠን እንዲደረጉ MCPS MCPDን ያበረታታል።

   c) እስራት ወይም ክስ የተመሠረተ መሆኑ ወይም የተጠረጠረው ድርጊት ተፈጽሟል የሚባለው በ MCPS ንብረት ውስጥ መሆኑ እንደታወቀ፣ ርእሰመምህር ወይም ሱፐርቫይዘር ከ MCPS Systemwide Child Abuse Contact፣ MCPS Department of Communications፣ እና County MDT ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር ለማህበረሰቡ አግባብነት ባለው ሁኔታ እንዲገለጽ ይደረጋል፣ እንዲሁም ለምሳሌ፦ የታሰረ(ች)ው ግለሰብ ቀደም ሲል ስለሠራ(ች)በት ቦታ ጭምር ለሌሎች ትምህርት ቤቶችም ማሳወቁ ተገቢነት እንደሚኖረው ይወሰናል።

2. MCPS ማንኛውንም የማህበረሰብ ማስታወቂያ ለመተግበር የሚከተሉትን እንዲያንፀባርቁ ጥረት ያደርጋል–

a) በማንሳቀል ወይም ቸልተኝነት ጥርጣሬ ተፅእኖ የተደረገባቸው ተማሪዎችና ቤተሰቦች ብህትውነትና ምስጢራዊነት ይጠብቃል ወይም ማንሳቀልን ወይም ቸልተኝነትን የሚመለከቱ ያልተፈቀዱ መዛግብትና ዘገባዎች ከማጋለጥ ይቆጠባል፤

b) በካውንቲ MDT ውስጥ ያሉ ተሳታፊ ወኪል ድርጅቶች ጥርጣሬዎቹን በት/ቤት ማህበረሰብ የሚገኙትን የሁሉንም ተማሪዎች ደህንነት በሚያረጋግጥ መንገድ በሚገባ እየያዙት መሆናቸውን ለማህበረሰቡ ያረጋግጣል፤ እና

c) የተጠረጠረው/ችዉ ኣጥቂ ተገቢ ህጋዊ ሂደት እንደሚያገኝ/ምታገኝ እና ከሜሪላንድ ህዝባዊ መረጃ ኣዋጅ ጋር የፀና ነው።

3. ማናቸውም ማህበረሰብ እንዲያውቀው የሚገለጽበት ደብዳቤ፣ ኢ-ሜይል፣ ወይም በኤሌክትሮኒክ የተቀረፀ ድምፅ ቅጂው ለ "MCPS Systemwide Child Abuse contact" መሰጠት አለበት።

4. በካውንቲ MDT የሚሳተፉ ወኪል ድርጅቶች፣ የተጠረጠረ ማንሳቀል ወይም ቸልተኝነት ምርመራዎቻቸውን በሚመለከት ከማህበረሰብ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ምላሽ በመስጠት የMCPS ሰራተኛ ኣባሎችን፣ እንደኣግባቡ፣ ለመደገፍ ተስማምተዋል።

## V. ምስጢራዊነት፣ መድህን፣ ከግብረመልስ መከላከል

A. በ Maryland ህግ፣ ማንም ሰው በቀና መንፈስ በደል ወይም ቸል መባልን (ተገቢውን እንክብካቤ አለማግኘትን) ሪፖርት ካደረገ/ች ወይም በማድረግ ከተሳተፈ/ች ወይም በምርመራ ወይም ከዛ ተከትሎ በመጣ የፍርድ ሂደት ከተሳተፈ/ች በሌላ ሁኔታ የበደልን ወይም ቸል መባልን ፣ ወይም በምርመራ ወይም ከዛ ተከትሎ በመጣ የፍርድ ሂደት በመሳተፍ ሊመጣ ከሚችል ከሲቭል (የፍትሃብሄር) ተጠያቂነት ወይም ከወንጀል ቅጣት ነጻ ይሆናል/ትሆናለች።

B. በሜሪላድ ህግ፣ ማንም የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ ወይም በጎ-ፈቃደኛ ሆነ ብሎ በማንሳቀልና ቸልተኛነት ዘገባ ማጨናገፍ ወይም ጠልቃ መግባት ኣይችልም። ይህን የሜሪላንድ ህግ የመጣስ ቅጣት ኣምስት ኣመት እስራት፣ የ$10,000 ቅጣት፣ ወይም ሁለቱም ነው።

C. የ MCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ እና በጎ-ፈቃደኞች በቀና መንፈስ ቀርበው ስለ ማንሳቀል ወይም ቸልተኝነት ዘገባ ሲያቀርቡ እና/ወይም የማንሳቀል ወይም ቸልተኝነት ምርመራ ውስጥ ሲሳተፉ፣ MCPS በነዚያ ምክንያት ሊደርስባቸው ከሚችል ከማስፈራራት፣ ወከባ፣ ወይም በቀል ሊጠብቃቸው ይጥራል።

D. ተማሪዎች የማንሳቀል ወይም ቸልተኝነት ተጠቂዎች ወይም ምስክሮች ሲሆኑ ወይም በቀና መንፈስ ቀርበው ስለ ማንሳቀል ወይም ቸልተኝነት ዘገባ ሲያቀርቡ እና/ወይም የማንሳቀል ወይም ቸልተኝነት ምርመራ ውስጥ ሲሳተፉ፣ MCPS በነዚያ ምክንያት ሊደርስባቸው ከሚችል ከማስፈራራት፣ ወከባ፣ ወይም በቀል ሊጠብቃቸው ይጥራል።

E. በሜሪላንድ ህግ የተጠረጠረ ማንሳቀል ወይም ቸልተኝነትን የሚመለከት የመዛግብት ወይም የዘገባዎች ያልተፈቀደ መጋለጥ የወንጀለኝነት ጥቃት ነው። በተጨማሪ፣ ሁሉም የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ እና በጎ-ፈቃደኞች ምንጩ እንዲገለፅ በህግ ካልተጠየቀ በስተቀር የዘጋቢውን ማንነት እንዲጠብቁ ይፈለግባቸዋል።

## VI. ሆን ብሎ/እያወቁ የማንሳቀል ወይም ቸልተኝነት ዘገባ ኣለማቅረብ ወይም ዘገባ ሲደረግ ጣልቃ መግባት የሚያስከትሏቸው ውጤቶች

A. ማንኛውም የ MCPS ሰራተኛ፣ በሙያዊ ችሎታው ለ MCPS በመስራት ላይ የሚገኝ፣የልጅ ማንሳቀል እና/ወይም ቸልተኝነት የሚጠረጥር እና እያወቀ ዘገባ ያላቀረበ፣ ወይም ሆን ብሎ ዘገባውን የሚከለክል ወይም ጣልቃ የሚገባ፣ ዲሲፕሊን ይወሰድበታል እገዳ ወይም ስንብትን ጨምሮ። የወንጀል ቅጣቶችን

እያወቁ ሪፖርት አለማድረግ እና በሚቀርብ ሪፖርት ላይ ሆን ተብሎ ጣልቃ መግባት/ማደናቀፍ በወንጀል የሚያስቀጣ መሆኑን የሜሪላንድ ህግ ይደነግጋል።

B. በተጨማሪ፣ በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ቦርድ ወይም በሌላ የስራ ፈቃድ ወይም የችሎታ የምስክር ወረቀት ሰጪ ቦርድ የተሰጠ ምስክርነት ሊታገድ ወይም ሊነሳ ይችላል፣ በሜሪላንድ ህግ በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት፣ COMAR 13A.12.05.02ን ጨምሮ።

C. ለ MCPS በመሥራት ላይ የሚገኝ ማናቸውም የ MCPS ኮንትራክተር፣ የልጅ ጉስቁልና እና ቸልተኝነትን እየተጠራጠረ(ች) እያወቀ(ች) ሪፖርት ካላደረገ(ች)፣ ወይም ሪፖርት እንዳይደረግ ሆን ብሎ ማደናቀፍ/ጣልቃ መግባት፣ አገልግሎትን እስከማቋረጥ የሚደርስ የዲስፕሊን እርምጃ ያስወዳል።

D. ማናቸውም ለ MCPS በመሥራት ላይ የሚገኝ/የምትገኝ በጎፈቃደኛ፣ የልጅ ጉስቁልና እና ቸልተኝነትን እየተጠራጠረ(ች) እያወቀ(ች) ሪፖርት ካላደረገ(ች)፣ ወይም ሪፖርት እንዳይደረግ ሆን ብሎ ማደናቀፍ/ጣልቃ መግባት፣ የበጎፈቃደኝነት አገልግሎትን ጠቀሜታ እስከማቋረጥ የሚደርስ የዲስፕሊን እርምጃ ያስወዳል።

## VII. በማይገባ ጾታዊ ተግባር ተጠርጣሪ ወይም የሚጠረጠር ሰው ለወደፊት የሥራ ተቀጣሪ እንዲሆን/እንድትሆን የተከለከሉ የድጋፍ አስተያየቶች

A. ማንም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኛ፣ ኮንትራክተር፣ ወይም ሥራ እየሠራ ያለ በጎፈቃደኛ፣ ግለሰቡ/ቧ ካወቀ(ች)፣ እና ሠራተኛ፣ ኮንትራክተር፣ ወይም በጎፈቃደኛ ከተማሪ ጋር ወይም ትንሽ ልጅ ጋር በወሲባዊ ምግባር ላይ መሳተፉ(ፏ)ን ለማመን የሚያስችል ምክንያት ካለ፣ አስተዳደራዊ እና የግል ፋይሎችን ከማስተላለፍ በስተቀር ስራ ለማስገኘት መርዳት እንደሌለባቸው የፌደራል ህግ ይደነግጋል።

1. ለመርዳት ወይም ለመተባበር የተከለከሉ አይነት ነገሮች የሚያካትቱት፣ በዚህ ብቻ የተወሰነ ባይሆንም ወደፊት ሥራ ለሚቀጥር ምስክርነት መስጠት ወይም ማስተላለፍ ክልክል ነው። ሠራተኛ፣ ኮንትራክተር፣ ወይም በጎፈቃደኛ ልጆችን ወይም ተማሪዎችን የሚያሳትፍም ሆነ የማያሳትፍ ሥራ የሚፈልግ/የምትፈልግ ቢሆንም እንኳ ድጋፍ መስጠት ክልክል ነው።

2. ሊወሰዱ የሚችሉት አስተዳደራዊ እርምጃዎች ያለውን የአሠራር ሂደት በመከተል የሚያካትተው፣ በዚህ ብቻ ባይወሰንም፣ የትራንስክሪፕት ቅጂውን፣ ወይም የቅጥር ቀን ማረጋገጫ የተለመደውን አስተዳደራዊ እና የግል ፋይሎችን ማስተላለፍ።

B. ይህ እገዳ በሥራ ሊውል የማይችለው –

1. ጉዳዩ በይፋ የተዘጋ እንደሆነ፣ ወይም ምርመራ ተደርጎ ለጉዳዩ በቂ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ያልተገኘ እንደሆነ፣

2. ሠራተኛው(ዋ)፣ ኮንትራክተር፣ ወይም በጎፈቃደኛ በተከሰሰ(ች)በት በስነምግባር ብልሹነት ከሆነ፣ እና ከተጠረጠረ(ች)በት ክስ ነፃ የሆነ(ች) ከሆነ፣ ካልሆነም ከቀረበበት ክስ ነፃ መሆኑ(ኗ) የተረጋገጠ ከሆነ፣ ወይም

3. ጉዳዩ ወይም ምርመራው ክፍት ሆኖ እያለ እና በአራት ዓመት ውስጥ ምንም ክስ ያልተመሠረተበ(ባ)ት ከሆነ።

C. ስለእነዚህ አይነት ተቀባይነት ያላቸው ወይም የተከለከሉ ሁኔታዎች ጥያቄዎች ያሏቸው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች OEELR ን ማነጋገር ይኖርባቸዋል።

## VIII. ከማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ጋር የተያያዙ ኣመፆች የሚያስከትሏቸው ውጤቶች

A. የሞንትጎመሪ ሠራተኛ በማጎሳቆል ወይም በቸልተኝነት መሣተፉ(ፏ)ን MCPS ካረጋገጠ ወይም የቦርድ ፖሊሲዎችን፣ የ MCPS ደንቦች/መመሪያዎችን፣ ኮንትራቶችን፣ ወይም በተጨማሪ የየሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሠራተኛ ስነምግባር ደምብ/ኮድ መተላለፉ(ፏ)ን ከታመነ፣ ግለሰቡ(ቧ) ከሥራ መታገድ ወይም እስከ መባረር ድረስ የዲስፐሊን እርምጃ ሊወሰድ ይችላል። ከዚህ ይበልጥ፣ በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ቦርድ ወይም ሌላ ፈቃድ ሰጪ አካል ወይም ሠርተፊኬት የሚሰጥ ቦርድ አማካይነት የተሰጡ ማናቸውም ሠርተፊኬቶች COMAR 13A.12.05.02 ጨምሮ በሜሪላንድ ህጋዊ ድንጋጌ መሠረት፣ ይታገዳሉ ወይም ይነጠቃሉ።

B. ኣንድ የ MCPS የስራ ተቋራጭ ወይም በጎ-ፈቃደኛ በማጎሳቆል ወይም በቸልተኝነት ተካትቷል/ተካታለች ወይም ኣለዝያ የቦርድ መመርያዎች፣ የMCPS ደንቦች፣ ወይም መመርያ፣ የ MCPS ሰራተኛ የስነምግባር ኮድን ጨምሮ፣ ጥሷል/ጥሳለች ብሎ MCPS ከወሰነ ግለሰቡ/ቧ የኣገልግሎቶች ወይም የበጎ-ፈቃደኛ ልዩ ጥቅሞች መቋረጥን ጨምሮ፣ እንደኣግባቡ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድበ(ባ)ታል።

## IX. የሙያ እድገት

A. MCPS፣ የካውንቲ MDT ተባባሪ ወኪል ድርጅቶችን ጨምሮ ከሀገራዊና ከኣካባቢ ወኪል ድርጅቶች የባለሙያ ድጋፍ ጋር፣ የMCPS ሰራተኞች ይህን ደንብ በመተግበር ላይ ተገቢ ሞያዊ እድገት/ስልጠና ያቀርባል።

1. ከተማሪዎች ጋር መስራት ከመጀመራቸው በፊት፣ ሁሉም ኣዳዲስ የMCPS ሰራተኞች የልጅ ወይም የደካማ ኣዋቂ ማጎሳቆልና ቸልተኝነት መለየት፣ ዘገባ ማቅረብ፣ እና መከላከል ኣስገዳጅ ስልጠና ይቀበላሉ። ሁሉም የMCPS ሰራተኞች ይህን የኣዲስ ተቀጣሪ ስልጠና መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ OEELR ዘገባዎች ይይዛል።

2. በእያንዳንዱ አዲስ የትምህርት ዓመት መጀመሪያ ላይ፣ በሥራ ላይ ያሉት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች በሙሉ ስለ ልጅ ማጎሳቆል እና ቸልተኝነት መረዳታቸውን እና ሪፖርት የማድረግ ፕሮቶኮል እውቀት ወቅታዊ ግንዛቤ እንዳላቸው ለማረጋገጥ ስልጠና ይወስዳሉ። ስልጠናዎች በድርጅቱ በተለያዩ ደረጃዎች ላይ ለሚገኙ ሰራተኞች ፍላጎቶች እንደሚስማሙ ሆነው በተለይ ተስተካክለው በግምባር ወይም በመስመር ላይ ትምህርት በማካተት ይዘጋጃሉ። እንደ አግባቡ፣ ስልጠናው ለተጠርጣሪ ኣመፀኞች ህጋዊ ሂደትንም ይመለከታል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች በሙሉ በየዓመቱ ተፈላጊውን ስልጠና ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ OEELR ሪኮርዶችን ይይዛል።

B. ለ MCPS የበጎፈቃድ ሠራተኞች እና ለኮንትራክተሮች እንዲሁም ለወላጆች እና ሌሎች የ MCPS ሰፊ ማህበረሰብ፣ ስለ ልጆች እና ተጋላጭ የሆኑ አዋቂ ሰዎችን መጎሣቆል እና ቸልተኝነት ግንዛቤ እና ሪፖርት አቀራረብ እና መከላከል ግንዛቤ፣ ስለ ቦርድ ፖሊሲዎች እና የ MCPS ደንቦች እና/ወይም ሌላ መመሪያ ጨምሮ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የሠራተኛ ስነምግባር ደንብ/ኮድ/MCPS Employee Code of Conductስለ እነዚህ ትኩረት የሚሰጥባቸው ጉዳዮች፣ በብሔራዊ እና የአካባቢ ኤክስፐርቶች ድጋፍ፣ የካውንቲ MDT አጋር ኤጀንሲዎችን ጨምሮ፣ MCPS አውደጥናቶችን፣ መርጃዎችን፣ እና በአውታረ-መረብ የስልጠና ሞድዎሎችን እንደየአግባቡ ያቀርባል።

C. በተጨማሪ፣ እነዚያ የ MCPS በጎፈቃደኞችና ስራ ተቋራጮች ወደ ተማሪዎች መዳረሻ ያላቸውና የሚገናኙ፣ በMCPS ሰራተኞች በቀጥታ ቁጥጥር ስር ባልሆኑበት ሁኔታዎች፣ ስልጠና መቀበላቸውን እንዲመሰክሩ ይፈለግባቸዋል እና/ወይም መረጃያዊ ቁሳቁሶች ገምግመዋል፣ እንደ ኣግባቡ፣ መጎሳቆልና ቸልተኝነትን መለየት፣ ዘገባ ማቅረብ፣ እና መከላከል፣ ለMCPS ሰራተኞች ከተሰጠው ከሞያዊ እድገት ይዘት ጋር የሚጣጣም። የምስክር ወረቀት ፎርሞቹን ቅጂዎች MCPS ይይዛል።

***ተዛማጅ ምንጮች፡-***

Elementary and Secondary Education Act of 1965 (ESEA), as amended by the Every Student Succeeds Act Section 8546 (20 U.S.C. §7926); *Annotated Code of Maryland*: Criminal Law Article §3-602.2, Education Article §6-113 and §6-113.2, Family Law Article, §§5-560, 5-561, 5-701, 5-702, 5-704, 5-705.2, 5-705, 5-706, 5-708, 14-303; Human Services Article, §1-202; *Code of Maryland Regulations* 07.02.07.04-.05, 07.02.07.19, 13A.12.05.02 and 13A.08.01.03

**የደንብ ታሪክ፡-** የቀድሞ ደንብ ቁ. 525-10፣ ዲሰምበር 17፣ 1980፣ እና የደንብ ቁ. 525-19፣ ዲሴምበር 30/1980፣ ኦክቶበር 1983 ተከልሷል፣ ዲሴምበር1986 ተከልሷል፣ ጃኑወሪ 23/1989 ተከልሷል፣ ኦገስት 5/2015 ተከልሷል፣ ጁላይ 24/2017 የይዘት ለውጥ ያልተደረገበት ክለሳ ተደርጓል፣ ጁላይ 18/2019 ተከልሷል።